# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት



## የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለስልጣን ከኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ጋር በተያያዘ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

የካቲት30/2009 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## ማውጫ

ማውጫ ........ I

ማጠቃለያ (EXECUTIVE SUMMERY) ........ I

ክፍል አንድ ........ 1

መግቢያ ........ 1

የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለስልጣን መስሪያ ቤት አመሰራረት ........ 1

የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ራዕይ፣ ተልኮ እና ዓላማ ........ 2

የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ አደረጃጀት እና የሰው ኃይል ........ 4

የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ ........ 4

11. የኢትዮጲያ ኢነርጂ ባለስልጣን መስሪያ ቤት በአዋጅ የተሰጠውን ተግባር ለማከናወን ከመንግስት በጀት የሚመደብለት ሲሆን ከ2006 እስከ 2008 በጀት እስከ ሚያዚያ ወር ድረስ የተመደበለት በጀትና የወጣው ወጪ በሚከተለው ሰንጠረዥ1. ተመልክቷል፡፡ **ሰንጠረዥ1. የበጀት ማነጻጸሪያ** ........ 4

የኦዲቱ ዓላማ ........ 4

ለኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አከባቢ (AUDIT AREA) ........ 5

የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎችና የመመዘኛ መስፈርቶች ........ 5

የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ ........ 6

የኢነርጂ ቁጠባና ብቃት የአሰራር ሥርዓት ሥዕላዊ መግለጫ/PROCESS DESCRIPTION/ ... 7

ምስል1. የኢነርጂ ቁጠባና ብቃት የአሰራር ሥርዓት ሥዕላዊ መግለጫ ........ 7

ክፍል ሁለት ........ 8

የኦዲት ግኝቶች ........ 8

2.1.የኢነርጂ ብቃት (ENERGY EFFICIENCY) ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ ስለመሆኑ 8

የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ደንብና መመሪያዎች ተዘጋጅቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤ ........ 8

የኢነርጂ ብቃት የመፈተሻ ስርዓት አውጥቶ ተግባራዊ ስለመደረጉ እና የኢነርጂ ብቃት መፈተሻ ላብራቶሪዎች መቋቋማቸውን በተመለከተ፤ ........ 9

ለኢነርጂ መጠቀሚያና ለኤሌክትሪክ አገልግሎት የሚውሉ ቴክኖሎጂዎች የአጠቃቀም ደረጃ (Standard) ተዘጋጅቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፡ ........................................ 9

የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ፕሮግራም መዘጋጀቱን በተመለከተ፤ .................................. 10

የኢነርጂ ብቃት ደረጃዎች ኮድ፣ የኢነርጂ ብቃት ማረጋገጫ ተለጣፊ ኮድ፣ የኢነርጂ ኦዲት ኮድ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፡ ........................................................ 11

ከፍተኛ ኢነርጂ ተጠቃሚዎች ጋር የኢነርጂ ብቃትን የሚያበረታታ የፈቃደኝነት ስምምነት መኖሩንና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤ ................................................ 12

በኢነርጂ ዘርፍ ለተሰማሩ ድርጅቶች እና ግለሰቦች የፈቃድ አሰጣጥ የአሰራር ስርዓት መኖሩን እና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤ ........................................................ 13

ከፍተኛ ኢነርጂ ተጠቃሚዎች የኢነርጂ አጠቃቀማቸውን አስመልክቶ ክትትልና ቁጥጥር መደረጉን በተመለከተ፤ ........................................................................................ 13

2.2 የኢነርጂ ቁጠባ (ENERGY CONSERVATION) ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ ስለመሆኑ ........................................................................................................ 14

የኢነርጂ መጠቀሚያ ቴክኖሎጂዎችን ለመለየትና አጠቃቀማቸውን ማወቅ የሚያስችል የመነሻ ጥናት (Baseline) መደረጉን በተመለከተ ........................................................ 14

የሀገሪቱ የኢነርጂ ፍላጎት፣ ጥቅም ላይ የዋለ እና ያልዋለ የኢነርጂ መጠን የሚታወቅ ስለመሆኑ በተመለከተ፤ ........................................................................................ 15

የኢነርጂ መጠቀሚያ ቴክኖሎጂዎችን ለገበያ ከመቅረባቸው በፊት የሚያሟሉት ደረጃ በየመሣሪያዎቹና ዕቃዎቹ መገለጹን በተመለከተ፤ ...................................................... 16

2.3 የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ስራዎችን ውጤታማ ለማድረግ ክትትልና ድጋፍ፣ ቅንጅታዊ አሰራር እና የመረጃ አያያዝ ስርዓት መኖሩና ተግባራዊ ስለመደረጉ ............................. 17

ከፍተኛ የኢነርጂ ተጠቃሚ አካላትን የኢነርጂ አጠቃቀም ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ከመርሃ-ግብሩ አንፃር የመገምገምና ውጤቱን ማሳወቅን በተመለከተ፡ ............................ 17

የኢነርጂ ፈንድ ተቋቁሞ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤ ......................................... 19

ከፍተኛ የኢነርጂ ተጠቃሚዎች የኢነርጂ ኦዲት ግኝት በተገኘባቸው ላይ የማስተካከያ እርምጃ መወሰዱን በተመለከተ፤ ........................................................................ 20

የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ሰርቶ ማሳያ በተመለከተ፤ .................................................. 22

በባለስልጣን መ/ቤቱ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባን በሚመለከት የሚነሱ ቅሬታዎች የአፈታት ስርዓት መኖሩንና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤ ........ 23

ክፍል ሶስት ........ 25

መደምደሚያ ........ 25

ክፍል አራት ........ 27

የማሻሻያ ሀሳቦች ........ 27

አባሪ 1 ........ 31

የኦዲት መመዘኛ መስፈርት ........ 31

አባሪ 2: የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለሥልጣን ድርጅታዊ መዋቅር ........ 34

አባሪ 3፡ ........ 35

በናሙና ተመርጠው የታዩት ከፍተኛ ኢነርጂ ተጠቃሚ ተቋማት ........ 35

ምስሎች

ምስል1. የኢነርጂ ቁጠባና ብቃት የአሰራር ሥርዓት ሥዕላዊ መግለጫ ........ 7

**<u>ሰንጠረዦች</u>**

ሰንጠረዥ1. የበጀት ማነጻጸሪያ ........ Error! Bookmark not defined.

## ማጠቃለያ (Executive Summery)

በሁለተኛ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዘመን በከፍተኛ ወጪ እየተገነቡ ካሉት ሜጋ ፕሮጀክቶች የኢነርጂ ግንባታ ዋነኛ በመሆኑ የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለስልጣን የኢነርጂ ቁጠባና ብቃት አፈጻጸምን ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን በማረጋገጥ በኦዲቱ ወቅት መረጃዎችን በመከለስ፣ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ኃላፊዎች ቃለ መጠይቅ በማድረግ እና የግንባታ ሂደቱን በአካል ባሉበት በማየት ከዚህ በታች የታዩትን ዋና ዋና ግኝቶች እና የተሰጡት የማሻሻያ ሀሳቦችን ታይተዋል፡፡

- ባለስልጣን መ/ቤቱ የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ደንብና መመሪያዎች (Energy Efficiency Rule and Regulation) ሊያዘጋጅና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ይሁን እንጂ የኢነርጂ ደንብና መመሪያዎች በረቂቅ ደረጃ የተዘጋጀ ቢሆንም ጸድቆ ተግባራዊ እንዳልተደረገ በኦዲት ወቅት ከተሰበሰበው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡
- ለኢነርጂ መጠቀሚያና ለኤሌክትሪክ አገልግሎት የሚውሉ ቴክኖሎጂዎች የአጠቃቀም ደረጃ (Standard) ሊያወጣና በሚመለከተው አካል በማጸደቅ ተግባራዊ መሆኑን ሊቆጣጠር ይገባል::
- ይሁን እንጂ ለኢነርጂ መጠቀሚያና ለኤሌክትሪክ አገልግሎት የሚውሉ ቴክኖሎጂዎች የአጠቃቀም ደረጃ (Standard) ያልወጣ መሆኑን በኦዲት ወቅት ከተሰበሰቡት መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡
- የኢነርጂ ፈንድ በአዋጅ ቁጥር 810/2006 አንቀጽ 23 መሰረት ሊቋቋምና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ በኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ዘርፍ ለሚሳተፉ የኢነርጂ ተጠቃሚ ተቋማት የቴክኒክና የፋይናንስ ድጋፍ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ይሁን እንጂ የኢነርጂ ፈንድ ባለመቋቋሙ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ዘርፍ ለሚሳተፉ ተቋማት የቴክኒክና የፋይናንስ ድጋፍ አለመደረጉን በኦዲት ወቅት ከተሰበሰበው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

በመሆኑም፡-

- ❖ ባለስልጣን መ/ቤቱ የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ደንብና መመሪያዎች (Energy Efficiency and Conservation Rule and Regulation) በአስቸኳይ በሚመለከተው አካል አጸዲቆ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ለኢነርጂ መጠቀሚያና ለኤሌክትሪክ አገልግሎት የሚውሉ ቴክኖሎጂዎች ኃይል ቆጣቢ እና ብቃት ያላቸው መሆኑን የሚለይበት የአጠቃቀም ደረጃ (Standard) አውጥቶ በሚመለከተው አካል በማጸደቅ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል::
- ባለስልጣን መ/ቤቱ ሁሉ አቀፍ የሆነ እና ሊተገበር የሚችል የረጅም፣ የመካከለኛ እና የአጭር ጊዜ የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ስትራቴጂ አዘጋጅቶ በሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት እና በኢነርጂ ባለሙያዎች በማስገምገም ተግባራዊ ሊያደርግ እና በየወቅቱ ውጤቱን ሊገመግም ይገባል፡፡

## ክፍል አንድ

### መግቢያ

1. ለአንድ አገር ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና አከባቢያዊ እድገት ኢነርጂ አንዱና የጀርባ አጥንት ነው፡፡ የዓለማችን ሀገራት የእድገት ምጣኔ መለኪያ ኢነርጂ አንዱ መሳሪያ ነው፡፡ ሀገራች መካከለኛ ገቢ ካላቸው የዓለም ሀገራት ተርታ ለመሰለፍ አቅዳ ዘርፈ ብዙ የግንባታ ፕሮጀክቶችን እያካሄደች ትገኛለች፡፡ ከእነዚህ ሜጋ የግንባታ ፕሮጀክቶች ውስጥ የኢነርጂ ግንባታ ፕሮጀክት ዋነኛው ነው፡፡ በመሆኑም እየተገነባ ያለውን ኢነርጂ ደህንነቱ የተጠበቀ፣ አስተማማኝ፣ ቀጣይነት ያለው የሀይል አቅርቦትን እንዲኖር በብቃት እና በቁጠባ መጠቀም ወሳኝ ነው፡፡

## የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለስልጣን መስሪያ ቤት አመሰራረት

2. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት የሀገሪቱን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት ለማፋጠን አጋዥ ለሆነው የኤሌክትሪክ አገልግሎት ለመስፋፋት ግንቦት 1986 ብሔራዊ የኢነርጂ ፖሊሲ በማውጣት ለተግባራዊነቱም በአዋጅ ቁጥር 86/1989 የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኤጀንሲ ተቋቁሞ ከ1992-2006 ዓ.ም ሲሰራ ቆይቷል፡፡
3. የቀድሞ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኤጀንሲ በአገሪቱ ላይ የሚታየውን የኤሌክትሪክ አቅርቦትና አጠቃቀም ችግር ማቃለል፣ ለተጠቃሚው ህዝብ የሚቀርበውን የኤሌክትሪክ አገልግሎት አስተማማኝና ኢኮኖሚያዊነቱን ማረጋገጥ፣ በኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት፣ ማስተላለፍና አጠቃቀም ምክንያት ሊፈጠር የሚችለውን የአከባቢ መራቆት ብክለት መከላከል የሚሉ የፖሊሲ አላማዎችን ይዞ ሲንቀሳቀስ ቆይቷል፡፡
4. በኢነርጂ አዋጅ ቁጥር 810/2006 የተሰጠውን የኢነርጂ ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት እንዲችል በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 308/2006 በአዲስ መልክ የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለሥልጣን ተቋቋመ፡፡

## የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ራዕይ፣ ተልኮ እና ዓላማ

### ራዕይ

5. በ2012 የቁጥጥር አቅምን በማሳደግ በኤሌክትሪክ አቅርቦትና አገልግሎት የተገልጋዮች እርካታ ስማንያ አምስት(85) በመቶ ተሟልቶ እንዲሁም የኢነርጂ አቅርቦትና ኢነርጂ አጠቃቀም ብቃትና ቁጠባን አስራ አምስት(15) በመቶ አድጎ ማየት፡፡

### ተልዕኮ

6. በኤሌክትሪክ ስራዎች ፈቃድ መስጠት የታሪፍ ፕሮፖዛል በማቅረብ፤ የአገልግሎት ደረጃ በማውጣት አገልግሎቱ አስተማማኝ፣ ፍትሀዊ እና ኢኮኖሚያዊ እንዲሆን በማድረግ እንዲሁም በኢነርጂ አቅርቦት እና አጠቃቀም ጥናት በማካሄድ የብቃት ደረጃ በማውጣት፣ የአህዝቦት ስራ በመስራ እና ፈቃድ በመስጠት ብቃትና ቁጠባን ማሳደግ፡፡

### አላማ

7. ጥራቱና አስተማማኝነቱ የተረጋገጠ በቂ የኤሌክትሪክ አቅርቦትና አገልግሎት እንዲኖር ለማስቻል ኢንቨስትመንትን የሚያበረታታ ግልፅና ፍትሀዊ የቁጥጥር ስርዓት በመዘርጋት መቆጣጠር፡፡

### የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ስልጣንና ተግባር

8. የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለስልጣ የአስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 810/2006 መሠረት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ተሰቶታል፣

- በዚህ አዋጅና በአዋጅ መሠረት በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት ፈቃድና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስጠትና ማደስ፣
- ማንኛዉም ባለፈቃድ ወይም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች እና በአዋጁ መሠረት የወጡ ደንቦችንና መመሪያችን አክብሮ እየሰራ መሆኑን መቆጣጠር፣ ይህ አዋጅ ወይም በዚህ አዋጅ መሰረት የወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎችን ተጥሰዉ ሲገኙም እንደጥፋቱ ክብደት ባለፈቃዱን ወይም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠውን ሰው በገንዘብ መቅጣት ወይም ፈቃዱን ማገድ ወይም መሰረዝ፣

- በባለፈቃዱ የሚቀርብለትን ከብሔራዊ ግሪዱ ጋር የተያያዘ ታሪፍ መገምገምና እንዲጸድቅ ለመንግስት የውሳኔ ሀሳብ ማቅረብ፤ ሲጸድቅም አፈፃፀሙን መቆጣጠር፤ ከብሔራዊ ግሪዱ ዉጭ የሆኑ ታሪፎችን አወሳሰን መመሪያ ማውጣትና አፈፃጸሙን መቆጣጠር፣
- የረጅም፣ የመካከለኛና የአጭር ጊዜ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ስትራቴጂና ፕሮግራም በአገር አቀፍ እንዲሁም በዘርፍ ደረጃ ማዘጋጀት እና አፈፃጸማቸን በየወቅቱ በሚቀርብለት ሪፖርቶች መሠረት መገምገም፣
- የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባን በብሔራዊ እና በዘርፍ ደረጃ ማስፋፋት፣
- የኢነርጂ ኦዲት ኮድ፣ የኢነርጂ ብቃት ደረጃዎች ኮድ፣ የኢነርጂ ብቃት ማረጋገጫ ተለጣፊ ምልክት ኮድ፣ የግሪድ ኮድ፣ የደንበኞች አገልግሎት አሰጣጥ ኮድ፣ የኢንስፔክሽን ኮድ፣ የአገልግሎት ጥራት ደረጃ ኮድ፤ የሕንፃ ኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ ኮድ፣ ቴክኒካል ስታንዳርድ ኮድ፣ እና ሌሎች ኮዶችን ማውጣት እና አፈጻጸማቸውንም መቆጣጠር፣
- የኤሌክትሪክ ኃይል ግዢ እና የኔትወርክ አገልግሎት ስምምነቶችን ማፅደቅ፣
- የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባን፣ የኢነርጂ ልማትን እና የኤሌክትሪክ ኃይል ንግድን ለማስፋፋት ከስልጠና ተቋማት እና ከአህጉራዊና ዓለም አቀፍ መድረኮች ጋር መተባበር፣
- የኢነርጂ ብቃት መፈተሻ ላብራቶሪዎችን ማቋቋምና የፍተሻ ስርዓቶችን ማውጣትና መተግበር፣
- የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ጥናትን፣ ልማትንና ሠርቶ ማሳየን እንዲሁም የቴክኖሎጂ ዝውውር ተግባራትን ማስፋፋትና ማስተባበር፣
- ከኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ጋር የተዛመዱ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ መተንተን፣ ማደራጀትና ማሰራጨት፣
- በዚህ አዋጅ መሰረት ቁጥጥር ሊደረግበት በሚገባ በማንኛውም ጉዳይ ላይ በሚመለከታቸው ወገኖች መካከል አለመግባባት በመከሰቱ የቀረበ አቤቱታን መስማት፣ ማጣራት እና አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘውም ማስማማት ወይም በግልግል መጨረስ፣
- በአዋጁ መሠረት በሚወጣ ደንብ የሚወሰኑ ፈቃድና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለመስጠትና ለማደስ እና ለሚሰጣቸው ሌሎች አገልግሎቶች የሚጠየቁ ክፍያዎችን እና የፈንዱን ገቢዎች መሰብሰብ፣

- እንደአስፈላጊነቱ ሥልጣንና ተግባሩን አግባብ ላላቸዉ የክልል አስፈጻሚ አካላት በውክልና ማስተላለፍና የአቅም ግንባታ ድጋፍ መስጠት፣

## የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ አደረጃጀት እና የሰው ኃይል

### ድርጅታዊ መዋቅር

9. ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በቦርድ የሚተዳደር ሆኖ ተጠሪነቱ ለውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር ነው፡፡ ተቋሙ በዋና ዳይሬክተር የሚመራ ሲሆን ሶስት ኮር ዳይሬክቶሬቶች፣ ስምንት የደጋፊ ዳይሬክቶሬቶች እንዲሁም ሁለት ጽ/ቤቶችን በመያዝ እንዲደራጅ ተደርጎ ተዋቅሯል፡፡ የባለስልጣኑ ድርጅታዊ መዋቅሩ **በአባሪ** (2) ተያይዟል፡፡

### የሰው ኃይል

10. ለባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በመዋቅር የተፈቀደው የሰው ኃይል ብዛት 165 ሲሆን እስከ ህዳር 2009 ዓ.ም ድረስ 75(45.45%) የሰው ኃይል በሥራ ላይ ይገኛል፡፡ ከዚህም ውስጥ ፕሮፌሽናል የሴት 30 እና የወንድ 23 በድምሩ 53 እንዲሁም ፕሮፌሽናል ያልሆኑ የሴት 7 እና የወንድ 15 በድምሩ 22 በአጠቃላይ የሴት 37 እና የወንድ 38 በድምሩ 75 ሠራተኞች አሉት፡፡

## የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ

11. የኢትዮጲያ ኢነርጂ ባለስልጣን መስሪያ ቤት በአዋጅ የተሰጠውን ተግባር ለማከናወን ከመንግስት በጀት የሚመደብለት ሲሆን ከ2006 እስከ 2008 በጀት እስከ ሚያዚያ ወር ድረስ የተመደበለት በጀትና የወጣው ወጪ በሚከተለው ሰንጠረዥ1. ተመልክቷል፡፡ **ሰንጠረዥ1. የበጀት ማነጻጸሪያ**

| በጀት ዓመት | ተፈቀደ በጀት | ስራ ላይ የዋለ በጀት | ሥራ ላይ የዋለው በጀት በመቶኛ |
|---|---|---|---|
| 2006 | 6,975,890 | 6,665,574 | 95.5% |
| 2007 | 13,559,217.66 | 12,759,357 | 94% |
| 2008 | 12,149,360 | 7,951,509 | 65.4% |

## የኦዲቱ ዓላማ

12. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ የኢነርጂ አገልግሎት ብቃትና ቁጠባ ኢኮኖሚያዊ፣ ውጤታማ እና ቀልጣፋ በሆነ መልኩ መከናወኑን መገምገም ሲሆን፣ በዚህ ዙሪያ የሚከሰቱትን

የአሰራር ክፍተቶችን ለይቶ በማውጣት የሚቀረፉበት የማሻሻያ ሃሳቦች ለማቅረብ ነው፡፡

## ለኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አከባቢ (Audit Area)

13. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ ፡

***"የኢትዮጲያ ኢነርጂ ባለስልጣን የኢነርጂ ብቃት(Energy Efficiency) እና ቁጠባ(Energy Conservation) አፈጻጸም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን መገምገም"***

የሚል ነው፡፡

## የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎችና የመመዘኛ መስፈርቶች

### የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች

14. ከላይ ለተመረጠው የኦዲት አካባቢ (Audit Area) ሶስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) ተዘጋጅተዋል፡፡ እነርሱም:-

1. የኢነርጂ ብቃት (Energy Efficiency) ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ መሆኑን መገምገም፣
2. የኢነርጂ ቁጠባ (Energy Conservation) ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ መሆኑን መገምገም እና
3. የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ስራዎችን ውጤታማ ለማድረግ)፣ ክትትልና ድጋፍ፣ ቅንጅታዊ አሰራር እና የመረጃ አያያዝ ስርዓት መኖሩን እና ተግባራዊ መደረጉን መገምገም

የሚሉ ናቸው፡፡

### የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria)


15. ከላይ ለተመረጡት ሶስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ለመመዘን የሚረዱ 32 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ተዘጋጅተዋል፡፡ የተዘጋጁት መመዘኛ መስፈርቶች በሚኒስቴር መ/ቤቱ አስተያየት እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡ የመመዘኛ መስፈርቶቹ በአባሪ (1) ተያይዘዋል፡፡

## የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

16. ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ማንዋል (Ethiopian Performance Audit Manual) እና ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ነው፡፡ የኦዲት ሽፋኑ ከ2006 እስከ 2008 ያለውን የሦስት በጀት ዓመት አፈጻጸም ነው፡፡ ለክዋኔ ኦዲቱ በተመረጡት የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች መሠረት መረጃዎቹ ተተንትነዋል፡፡ እንዲሁም ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎችና ባለሙያዎች ጋር ቃለ መጠይቅ ተደርጓል፡፡

17. ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በባለስልጣን መ/ቤቱ ሲሆን ዋና ባለድሻ አካላት የኢትዮጵያ የውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል፣ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት እንዲሁም በናሙና ተመርጠው የታዩት ከፍተኛ ኢነርጂ ተጠቃሚ ተቋማት በዘጠኝ ፋብሪካዎች፣ በአምስት ሆስፒታሎች እና በአምስት ሆቴሎች በአካል በመገኘት ለሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ፣ ከኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ጋር ተያያዥነት ላያቸውን መረጃዎች ጠይቆ በመከለስ እና የኢነርጂ አጠቃቀማቸውንና አያያዛቸውን አፈጻጸም በአካል በመመልከት ነው፡፡ (የታዩት ተቋማት ዝርዝር በአባሪ 3 ተያይዘዋል)

የኢነርጂ ቁጠባና ብቃት የአሰራር ሥርዓት ሥዕላዊ መግለጫ/Process Description/




ምስል1. የኢነርጂ ቁጠባና ብቃት የአሰራር ሥርዓት ሥዕላዊ መግለጫ

## ክፍል ሁለት

## የኦዲት ግኝቶች

### 2.1. የኢነርጂ ብቃት (Energy Efficiency) ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ ስለመሆኑ

የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ደንብና መመሪያዎች ተዘጋጅቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤

18. ባለስልጣን መ/ቤቱ የኢነርጂ አዋጅ ቁጥር 810/2006 ላይ የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን ለማስፈጸም የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ (Energy Efficiency and conservation) ደንብና መመሪያዎች ሊያዘጋጅና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
19. ይሁን እንጂ አዋጁን ለማስፈጸም የሚረዱ የኢነርጂ ብቃትና ቁጣባን የሚመለከቱ ደንብና መመሪያዎች በረቂቅ ደረጃ የተዘጋጁ ቢሆንም ያልጸደቁ መሆኑ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡
20. ስለጉዳዩ የባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው የኢነርጂ ስራዎች ደንብ ረቂቅ ከአዋጁ ጎን ለጎን የተዘጋጀ ቢሆንም እስካሁን አለመፅደቁ እና ቁጥር ወመኤሚ 59/05/112 በተጻፈው ደብዳቤ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ህዳር 05 ቀን 2009 ዓ.ም በባለድርሻ አካላት አስተያየት የተሰጠበት በቀድሞ ፍትህ ሚኒስቴር ታይቶ በተሰጠው አስተያየት መሰረት መላኩን በቀረበላቸው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ያላቸውን አስተያየት ገልጸዋል፡፡
21. የኢነርጂ ብቃት እና የኢነርጂ ቁጠባ ደንብና መመሪያዎች ጸድቆ ተግባራዊ አለመደረጉ በአዋጅ ቁጥር 810/2006 የኢነርጂ አዋጁን እና ለባለስልጣኑ መ/ቤት የተሰጠውን የኢነርጂ ተግባርና ኃላፊነቱን እንዳይወጣ እንቅፋት ሆኗል፡፡

## የኢነርጂ ብቃት የመፈተሻ ስርዓት አውጥቶ ተግባራዊ ስለመደረጉ እና የኢነርጂ ብቃት መፈተሻ ላብራቶሪዎች መቋቋማቸውን በተመለከተ፤

22. ባለስልጣን መ/ቤቱ የኢነርጂ ብቃት የመፈተሻ ስርዓት ሊያወጣና ሊተገብር ይገባል፡፡ ባለስልጣን መ/ቤቱ የኢነርጂ ብቃት መፈተሻ ላብራቶሪዎችን ሊያቋቁም ይገባል፡፡

23. ይሁን እንጂ ባለስልጣን መ/ቤቱ የኢነርጂ ብቃት መፈተሻ ስርዓት ያልዘረጋ እና የኢነርጂ ብቃት መፈተሻ ላብራቶሪዎችን እንዳላቋቋመ በኦዲት ወቅት ከተሰበሰበው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

24. ስለጉዳዩ የባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው አዋጅ ማስፈጸሚያ ደንብ ባለመጽደቁ የኢነርጂ ብቃት የመፈተሻ ስርዓት እንዳልተዘረጋ እና የኢነርጂ ብቃት መፈተሻ ላብራቶሪዎችን ለማቋቋም እንዳልተቻለ በቀረበላቸው ማጠቃለያ ጥያቄ ላይ ገልጸዋል፡፡

25. የኢነርጂ ብቃት መፈተሻ ስርዓት ባለመዘርጋቱ እና የኢነርጂ ብቃት መፈተሻ ላብራቶሪዎችን አለመቋቋሙ ብቃት ያላቸው እና የሌላቸው የኢነርጂ መጠቀሚያ ማሽነሪዎች፣ መሳሪያዎች እና ቴክኖሎጂ እቃዎች ተለይተው እንዳይታወቁ ከማድረጉማ በላይ ወጪ ቆጣቢ እና ኃይል ቆጣቢ የሆኑት ብቻ ሥራ ላይ እንዲሆኑ ማድረግን አዳጋች አድርጎታል፡፡

## ለኢነርጂ መጠቀሚያና ለኤሌክትሪክ አገልግሎት የሚውሉ ቴክኖሎጂዎች የአጠቃቀም ደረጃ (Standard) ተዘጋጅቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፡

26. ለኢነርጂ መጠቀሚያና ለኤሌክትሪክ አገልግሎት የሚውሉ ቴክኖሎጂዎች የአጠቃቀም ደረጃ (Standard) ሊያወጣና በሚመለከተው አካል በማጸደቅ ተግባራዊ መሆኑን ሊቆጣጠር ይገባል::

27. ይሁን እንጂ

- ለኢነርጂ መጠቀሚያና ለኤሌክትሪክ አገልግሎት የሚውሉ ቴክኖሎጂዎች የአጠቃቀም ደረጃ (Standard) ያልወጣ መሆኑን፣

- በሀገር ውስጥ የሚመረቱ የኤሌትሪክ መጠቀሚያ መሳሪያዎች ደረጃ ከአምራቾች ጋር በመወያየት ደረጃ እንዲኖራቸው ለማስቻል በባለሥልጣን መ/ቤቱ በ2006 በጀት ዓመት የተያዘው እቅድ ተግባራዊ አለመደረጉ፣ እንዲሁም
- በሀገር ውስጥ ለሚመረቱ የኤሌክትሪክ ምጣዶችና ምድጃዎች (Minimum Energy Efficiency Standard) እየተዘጋጀ ቢሆንም የአመራረት መመሪያ ግን አለመዘጋጀቱን፣

በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

28. ስለሁኔታው የባለስጣን መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሀገሪቱ በርካታ የኤሌትሪክ ዕቃዎች የምርት ደረጃ በኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ በኩል መውጣቱንና ለጊዜው ያለው የምርት ደረጃ እንደሆነ እንዲሁም የኢነርጂ ብቃት ደረጃ ግን የወጣላቸው መሳሪያዎች እንደሌሉ በቀረበላቸው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ አስተያየታቸውን ገልፀዋል፡፡

29. ለኢነርጂ መጠቀሚያና ለኤሌክትሪክ አገልግሎት የሚውሉ ቴክኖሎጂዎች የአጠቃቀም ደረጃ (Standard) አለመውጣቱ በገበያ ላይ ያለው የኤሌትሪክ ዕቃዎች የምርት እና ቴክኖሎጂዎች የአጠቃቀም ደረጃቸው እንዳይታወቅ፣ ከፍተኛ ብቃት ያላቸው እና የሌላቸው ለይቶ ለማወቅ እና ኢነርጂ ቆጣቢ ሆኑ መሳሪያዎችን ለማበረታታትና ድጋፍ ለማድረግ አዳጋች ያደርጋል፡፡

## የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ፕሮግራም መዘጋጀቱን በተመለከተ፤

30. በባለስልጣን መ/ቤቱ በጥናት የተደገፈ የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ፕሮግራም ሊዘጋጅ ይገባል፡፡ ፕግራሙም የትግበራ መርሀ ግብር ተዘጋጅቶለት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ በተጨማሪም የፕሮግራሙ አፈጻጸም በየጊዜው ሊገመገም እና ያስገኘው ዉጤት ሊለካ ይገባል፡፡

31. ይሁን ኢንጂ የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ፕሮግራም አለመዘጋጀቱን በኦዲት ወቅት ከተከለሰው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

32. ስለጉዳዩም የባለስልጣን መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በባለስልጣን መ/ቤቱ የኢነርጂ ብቃት እና ቁጣባ ፕሮግራም ያልተቀረጸ ነገር ግን ለሀገር አቀፍ ፕሮግራም ዝግጅት የሚሆኑ ጥናቶች በረቂቅ ደረጃ የተዘጋጁ መሆኑን

በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ እና ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

33. የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ፕሮግራም ባለመቀረጹ በሀገር ዓቀፍ ደረጃ የሁለተኛው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዘመን የታቀዱ እና በባለስልጣኑን መ/ቤቱ እንዲተገበሩ የተጣሉ ግቦች እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 810/2006 የተሰጠውን የኢነርጂ ተግባርና ኃላፊነቱን እንዳይወጣ እንቅፋት ሊሆን ይችላል፡፡

## የኢነርጂ ብቃት ደረጃዎች ኮድ፣ የኢነርጂ ብቃት ማረጋገጫ ተለጣፊ ኮድ፣ የኢነርጂ ኦዲት ኮድ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፡

34. ባለስልጣን መ/ቤቱ የኢነርጂ ብቃት ደረጃዎች ኮድ፣ የኢነርጂ ብቃት ማረጋገጫ ተለጣፊ ኮድ፣ የኢነርጂ ኦዲት ኮድ ሊያወጣና አፈፃፀሙንም ሊከታተል ይገባል፡፡

35. ይሁን እንጂ የኢነርጂ ብቃት ደረጃዎች ኮድ፣ የኢነርጂ ብቃት ማረጋገጫ ተለጣፊ ኮድ፣ የኢነርጂ ኦዲት ኮድ ያልወጣ መሆኑን በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

36. ስለጉዳዩ የባለስልጣን መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው ተጠይቀው የተለያዩ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ስራዎችን ተግባራዊ ለማድረግ አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን እና ኮዶችን በረቂቅ ደረጃ እንዳዘጋጁ ሆኖም ግን የኢነርጂ ደንቡ ባለመጽደቁ ተግባራዊ ለማድግ እንዳልቻሉ እንዲሁም የኢነርጂ ብቃት ማረጋገጫ ተለጣፊ ኮድ እየተሰራ መሆኑንና ተግባራዊ ለማድረግ ለህዝብ የማስተዋወቅ ስራ ላይ እንደሆኑ፣ የኢነርጂ ኦዲት የፈቃድ አሰራር መመሪያ ያልተዘጋጀ ነገር ግን የኢነርጂ ኦዲት ጋይድላይን የተዘጋጀ መሆኑን በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡ ኃላፊዎቹ ይህን ምላሽ ቢሰጡም ተዘጋጀ የተባለው የኢነርጂ ኦዲት ጋይድላይን ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ባለመቅረቡ መዘጋጀቱን ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

37. የኢነርጂ ብቃት ደረጃዎች ኮድ፣ የኢነርጂ ብቃት ማረጋገጫ ተለጣፊ ኮድ፣ የኢነርጂ ኦዲት ኮድ አለመውጣቱ በገበያ ላይ ያለው የኤሌትሪክ ዕቃዎች የምርት እና ቴክኖሎጂዎች የአጠቃቀም ደረጃቸው እንዳይታወቅ እና ተጠቃሚው በቀላሉ ኢነርጂ ቆጣቢ መሳሪያዎችን እንዳይለዩ፣ እንዲሁም የኢነርጂ ኦዲት ኮድ አለመዘጋጀቱ የከፍተኛ ኢነርጂ ተጠቃሚ የሆኑ ተቋማትን ኢነርጂ ኦዲት ለማከናወን አዳጋች ያደርገዋል፡፡

## ከፍተኛ ኢነርጂ ተጠቃሚዎች ጋር የኢነርጂ ብቃትን የሚያበረታታ የፈቃደኝነት ስምምነት መኖሩንና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤

38. ባለስልጣኑ በብሄራዊ ደረጃ ከከፍተኛ ኢነርጂ ተጠቃሚዎች ጋር የኢነርጂ ብቃትን የሚያበረታታ የፈቃደኝነት ስምምነት በመግባት ስምምነቱን ተግባራዊ ሊያደረግ ይገባል፡፡ በተጨማሪም በስምምነቱን በማይፈፅሙት ላይ በስምምነቱ መሰረት እርምጃ የሚወሰድበት ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

39. ይሁን እንጂ ከፍተኛ ኢነርጂ ተጠቃሚዎች ጋር የኢነርጂ ብቃትን የሚያበረታታ የተሻለ የኢነርጂ አጠቃቀም ያላቸው ተቋማት የፈቃደኝነት እንዲሁም ኃይል አባካኝ ወይም የኃይል ብክነት የሚታይባቸው ተቋማት የአስገዳጅነት ስምምነቶች የማያደረጉ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡ ስለጉዳዩ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ዳይሬክቶሬት ተጠይቀው ከከፍተኛ ኃይል ተጠቃሚ የሆኑ ኢንዳስትሪዎች፣ ሆስፒታሎች እና ሆቴሎች ጋር ኃይል አባካኝ የሆኑት አስገዳጅ እና የተሻለ አጠቃቀም ያላቸውን ተቋማት የፍቃደኝነት የኢነርጂ ቁጠባ ስምምነት ያልተደረገ ሲሆን ይህ የሆነበት ምክንያት የኢነርጂ ደንብ ባለመጽደቁ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

40. በናሙና ተመርጠው የታዩት ተቋማት የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው ከኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለስልጣን ጋር ኢነርጂን አስመልክቶ የተደረገ ስምምነት እንደሌለና ባለስልጣን መ/ቤቱ መኖሩንም የማያውቁ እንዳሉ፣ እንዲሁም ኃይል አባካኝ የሆኑና ብቃት የሌላቸው ማሽነሪዎች፣ መሳሪያዎች፣ ጀኔሬተሮች እንዲሁም አምፖሎች እየተጠቀሙ እንደሆነና ይህ የሆነበት ምክንያት የግንዛቤ እጥረት መሆኑን በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ገለጸዋል፡፡

41. ስለሁኔታው የባለስልጣን መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው የኢነርጂ ደንብ ባለመፅደቁ የአስገዳጅ ስምምነት አሰራር ተግባራዊ እንዳልተደረገ ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ አስተያየታቸውን ገልፀዋል፡፡

42. ከፍተኛ ኢነርጂ ተጠቃሚዎች የፈቃደኝነት እንዲሁም የአስገዳጅነት ስምምነቶች ባለመደረጉ በፈቃደኝነት እና ኃይል አባካኞች በማስገደድ ላይ የተመሰረተ የኢነርጂ ቁጠባ ስርዓት እንዳይኖር ከማድረጉም በተጨማሪ መቆጠብ የሚገባው የኢነርጂ መጠን እንዳይቆጠብ እና የሀገርቱ ውስን የኢነርጂ መጠን በአግባብ ስራ ላይ እንዳይውል አድርጓል፡፡

## በኢነርጂ ዘርፍ ለተሰማሩ ድርጅቶች እና ግለሰቦች የፈቃድ አሰጣጥ የአሰራር ስርዓት መኖሩን እና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤

43. በአገሪቱ ውስጥ ኤሌክትሪክ በማማንጨት፣ በማስተላለፍ በማከፋፈል እና በመሸጥ ስራ ላይ ለተሰማሩ የፈቃድ አሰጣጥ የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ የኢነርጂ ኦዲተሮችንና የኢነርጂ ኦዲት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች (ኩባንያዎች) የፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ ሊዘጋጅ እና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

44. ይሁን እንጂ ኤሌክትሪክ በማማንጨት፣ በማስተላለፍ በማከፋፈል እና በመሸጥ ስራ ላይ ለተሰማሩ የፈቃድ የመስጠት ስራ እየተሰራ እንዳልሆነ እንዲሁም ለኢነርጂ ኦዲተሮችንና የኢነርጂ ኦዲት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች (ኩባንያዎች) የፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ ያልተዘጋጀ እና ፈቃድም እየተሰጠ እንዳልሆነ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

45. ስለሁኔታው የባለስልጣን መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው የኢነርጂ አዋጅ ማስፈፀሚያ ደንብ እንደፀደቀ ስራ ላይ ሊውል የሚችል ረቂቅ የፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ ተዘጋጅቶ እንደምገኝ በቀረበላቸው መጠይቅ እና ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

46. የኤሌክትሪክ በማማንጨት፣ በማስተላለፍ በማከፋፈል እና በመሸጥ ሥራ ላይ እና እና በኢነርጂ ኦዲት ሥራ ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ አለመዘጋጀቱ በዘርፉ ለሚሰማሩ ለሚፈልጉ ባለሀብቶችና ባለሙያዎች ችግር የሚፈጥር እና የኢነርጂ ዘርፍ እንዳድግ የራሱን አሉታዊ ተጽዕኖ ይፈጥራል፡፡

## ከፍተኛ ኢነርጂ ተጠቃሚዎች የኢነርጂ አጠቃቀማቸውን አስመልክቶ ክትትልና ቁጥጥር መደረጉን በተመለከተ፤

47. ከፍተኛ ኢነርጂ ተጠቃሚዎች የኢነርጂ አጠቃቀማቸው የተሻለ እንዲሆን ብቃት ያላቸውን የኢነርጂ ቴክኖሎጂዎችን እንዲጠቀሙ ባለስልጣኑ የቁጥጥር እና የክትትል ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡

48. ይሁን ኢንጂ ከፍተኛ ኢነርጂ ተጠቃሚዎች የኢነርጂ አጠቃቀማቸው የተሻለ እንዲሆን ብቃት ያላቸውን የኢነርጂ ቴክኖሎጂዎችን እንዲጠቀሙ ባለስልጣኑ የቁጥጥር እና የክትትል ስራ እንደማይሰራ በኦዲቱ ወቅት የታዩት ተቋማት በርካታ

ኃይል ቆጣቢ ያልሆኑ እና ብቃት የሌላቸው ማሽነሪዎች፣ መሳሪያዎች፣ ጀኔሬተሮች እንዲሁም አምፖሎች ከግንዛቤ እጥረት የተነሳ እየተጠቀሙ እንደሚገኙ በኦዲቱ ወቅት ለማውቅ ተችሏል፡፡ በናሙና ተመርጠው የታዩት ተቋማት የስራ ኃልፊዎች ተጠይቀው የኢነርጂ አጠቃቀማቸው የተሻለ እንዲሆን ብቃት ያላቸውን የኢነርጂ ቴክኖሎጂዎችን እንዲጠቀሙ ከባለስልጣኑ የክትትል እና የቁጥጥር ሰራ የማይሰራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

49. ስለጉዳዩ የባለስጣን መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በተመረጡ ኢንዱስትሪዎችና አገልግሎት ሰጪዎች ላይ የቅኝት ኢዲት እና ዝርዝር ኢዲት እየተሰራ እንደሚገኝና በቁጠባ ላይም የአህዝቦት ስራ እየሰሩ እንደሚገኙ በቀረበላቸው መጠይቅ እና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

50. ኃላፊዎቹ ይህን ከላይ የተጠቀሰውን አስተያየት ቢሰጡም በጉዳዩ ዙሪያ እየሰሩ ስለመሆኑ እና ያስገኘው ውጤት የሚያስረዳ ማስረጃ ባለመቅረቡ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

51. ከፍተኛ ኢነርጂ ተጠቃሚዎች የኢነርጂ አጠቃቀማቸው የተሻለ እንዲሆን ብቃት ያላቸውን የኢነርጂ ቴክኖሎጂዎችን እንዲጠቀሙ ባለስልጣኑ የቁጥጥር እና የክትትል ስራ አለመሰራቱ፣ የኢነርጂ ተጠቃሚዎች ኃይል ቆጣቢ ያልሆኑ እና ብቃት የሌላቸው ማሽነሪዎች፣ መሳሪያዎች፣ ጀኔሬተሮች እንዲሁም አምፖሎች እንዲጠቀሙ እና ኢነርጂ እንዳይቆጥቡ አድርጓል፡፡

## 2.2 የኢነርጂ ቁጠባ (Energy Conservation) ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ ስለመሆኑ

### የኢነርጂ መጠቀሚያ ቴክኖሎጂዎችን ለመለየትና አጠቃቀማቸውን ማወቅ የሚያስችል የመነሻ ጥናት (Baseline) መደረጉን በተመለከተ

52. ባለስልጣን መ/ቤቱ የኢነርጂ መጠቀሚያ ቴክኖሎጂዎችን ለመለየትና የኢነርጂ አጠቃቀምን ማወቅ የሚያስችል የመነሻ ጥናት (Baseline) ሊያካሂድ እና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

53. ይሁን እንጂ ኃይል ቆጣቢ የሆኑ መሳሪያዎችን እና የኢነርጂ መጠቀሚያ ቴክኖሎጂዎችን ለመለየትና አጠቃቀማቸውን ማወቅ የሚያስችል የመነሻ ጥናት (Baseline) አለመደረጉን በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

54. ስለሁኔታው የባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው ከንግድ ሚኒስቴርና ከጉምርክ ባለስልጣን ጋር በመተባበር ኃይል አባካኝ የሆኑ ዕቃዎችን ከገበያ እንዲወጡ በማድረግ በምትካቸው ኃይል ቆጣቢ እቃዎች እንዲስፋፉ ጥረት እየተደረገ እንደሆነ እና ብሮሸሮችን እያሳተሙ ለህብረተሰቡ የሚያስተዋውቁበት ሁኔታ ቢኖርም ግን የኢነርጂ አጠቃቀም ደረጃ እንዳልተዘጋጀ እና የተደረገ የመነሻ ጥናት አለመኖሩን ገልፀው በሌላ መልኩ በኤሌክትሪክ ዘርፍ ሊቆጠብ የሚችል የኢነርጂ መጠንን የሚጠቁም Base Line ጥናትና ሊወሰዱ የሚችሉ ልዩ ልዩ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ እርምጃዎች ተጠንተዋል ነገር ግን ተግባራዊ አለመሆናቸውን በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ አስተያየታቸውን ገልጸዋል፡፡

55. የኢነርጂ መጠቀሚያ ቴክኖሎጂዎችን ለመለየትና አጠቃቀማቸውን ማወቅ የሚያስችል የመነሻ ጥናት (Baseline) አለመደረጉ በገበያ ላይ ያለው የኤሌትሪክ ዕቃዎች የምርት እና ቴክኖሎጂዎች የአጠቃቀም ደረጃቸው ስለማይታወቅ ከፍተኛ ብቃት ያላቸው እና የሌላቸው ለይቶ ለማወቅ አዳጋች ስለሚያደርገው ተጠቃሚው የሚገዛቸው የኢነርጂ መጠቀሚያ ማሽነሪዎች፣ መሳሪያዎች እና ቴክኖሎጂ እቃዎች ኃይል ቆጣቢ እና ወጪ ቆጣቢ መሆናቸውን ማረጋገጥ እንዳይችሉ ያደርጋል፡፡

## የሀገሪቱ የኢነርጂ ፍላጎት፣ ጥቅም ላይ የዋለ እና ያልዋለ የኢነርጂ መጠን የሚታወቅ ስለመሆኑ በተመለከተ፤

56. የሀገሪቱ የኢነርጂ ፍላጎት፣ የተመረተ፣ ጥቅም ላይ የዋለ እና ያልዋለ የኢነርጂ መጠን በባለስልጣን መ/ቤቱ ሊታወቅ ይገባል፡፡

57. ይሁን እንጂ በባለስልጣን መ/ቤቱ የሀገሪቱ የኢነርጂ ፍላጎት፣ የተመረተ ጥቅም ላይ የዋለ እና ያልዋለ የኢነርጂ መጠን የማይታወቅ መሆኑ በኦዲት ወቅት ከተሰበሰበው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ስለጉዳዩ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ዳሬክቶሬት ተጠይቀው የሀገሪቱ የኢነርጂ ፍላጎት፣ ጥቅም ላይ የዋለ እና ያልዋለ የኢነርጂ መጠን በባለስልጣኑ መ/ቤት እንደማይታወቅ ምክንያት ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ

ኃይል እና ኤሌክትሪክ አገልግሎት ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሰራር ጠንካራ ባለመሆኑ ነው በማለት በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

58. ስለሁኔታው የባለስልጣን መ/ቤቱ የስራ ኃላፊ ተጠይቀው በኤሌትሪክ ዘርፍ ሊቆጠብ የሚችል የኢነርጂ መጠንን የሚጠቁም Base Line ጥናት ተጠንተዋል በማለት በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ አስተያየታቸውን የገለፁ ቢሆንም ተጠንቷል የተባው ጥናት ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ መረጃው አልቀረበም፡፡

59. የሀገሪቱ የኢነርጂ ፍላጎት፣ የተመረተ፣ ጥቅም ላይ የዋለ እና ያልዋለ የኢነርጂ መጠን ባለመታወቁ መቆጠብ የሚገባንን የኢነርጂ መጠን እንዳንቆጥብ እንቅፋት ከመሆኑም በተጨማሪ የሚቆጥበው የሚፈልግው የኢነርጂ መጠን እንዳይታወቅ ያደርጋል፡፡

## የኢነርጂ መጠቀሚያ ቴክኖሎጂዎችን ለገበያ ከመቅረባቸው በፊት የሚያሟሉት ደረጃ በየመሣሪያዎቹና ዕቃዎቹ መገለጹን በተመለከተ፤

60. ኢነርጂ ቆጣቢ የሆኑ የኢነርጂ መጠቀሚያ ቴክኖሎጂዎችን ለገበያ ከመቅረባቸው በፊት የሚያሟሉት ደረጃ ሊታወቅ ይገባል፡፡ ከታወቀም በኋላ በየመሳሪያዎቹና ዕቃዎቹ ላይ ደረጃቸውን የሚገልጽ ግልጽ የተለጣፊ ምልክት ተዘጋጅቶ እንዲለጠፍ፣ እና የተለጣፊ ምልክቱንም ለአቅራቢዎቹ የመጠቀም መብት የሚያረጋግጥ ፈቃድ ሊሰጥ ይገባል፡፡

61. ይሁን እንጂ ኢነርጂ ቆጣቢ የሆኑ የኢነርጂ መጠቀሚያ ቴክኖሎጂዎችን ለገበያ ከመቅረባቸው በፊት የሚያሟሉት ደረጃ የማይታወቅ እና የሚያሟሉት የደረጃ ምልክትን የሚገልጽ ተለጣፊ ምልክት ተዘጋጅቶ በየመሣሪያዎቹና ዕቃዎቹ ላይ ደረጃቸውን እንዲለጥፉ ለማድረግ የተለጣፊ ምልክት መጠቀሚያ ለአቅራቢዎቹ ፈቃድ እንዳልተሰጠ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

62. ስለሁኔታው የባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው የኢነርጂ ብቃት ተለጣፊ ምልክት አሰራር (ኮድ) ደረጃ ለተመረጡ ዕቃዎች እየተሰራ ሲሆን ለኤሌትሪክ ምጣድ የሚሆን የተለጣፊ ምልክት አሰራር በዝግጅት ላይ መሆኑን እና በቀጣይም ለኤሌትሪክ ሞተር እና ለኤሌትሪክ ምድጃ ተመሳሳይ ስራ ለመስራት ቅድመ ዝግጅት እያደረጉ መሆኑን ለቀረበላቸው መጠይቅ እና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

63. ኢነርጂ ቆጣቢ የሆኑ የኢነርጂ መጠቀሚያ ቴክኖሎጂዎችን ለገበያ ከመቅረባቸው በፊት የሚያሟሉት ደረጃ ተጠቃሚዎች በግልጽ በሚረዱት መልክ ደረጃቸውን የሚገልጽ የተለጣፊ ምልክት እንዲለጥፉ አለመደረጉ እና ለአቅራቢዎቹ ኢነርጂ ቆጣቢ መሳሪያዎች ማቅረባቸቸው እየተረጋገጠ የተለጣፊ ምልክት ፈቃድ አለመሰጠቱ ህብረተሰቡ ኃይል ቆጣቢ ያልሆኑ እና ብቃት የሌላቸው የኢነርጂ መጠቀሚያ ዕቃዎች እንዲጠቀሙ ለማድረግ የራሱን አሉታዊ ተጽዕኖ ይፈጥራል፡፡

## 2.3 የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ስራዎችን ውጤታማ ለማድረግ ክትትልና ድጋፍ፣ ቅንጅታዊ አሰራር እና የመረጃ አያያዝ ስርዓት መኖሩና ተግባራዊ ስለመደረጉ

### ከፍተኛ የኢነርጂ ተጠቃሚ አካላትን የኢነርጂ አጠቃቀም ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ከመርሃ-ግብሩ አንፃር የመገምገምና ውጤቱን ማሳወቅን በተመለከተ፡

64. ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ከከፍተኛ ኢነርጂ ተጠቃሚዎች ጋር በአዋጅ ቁጥር 810/2006 አንቀጽ 22 መሰረት የኢነርጂ አጠቃቀም የፈቃደኝነት ስምምነት ሊፈራረም ይገባል፡፡ በስምምነቱ መሰረት በየዘርፉ (በኢንዱስትሪዎች፣ ሆቴሎች፣ ሆስፒታሎች እና ሌሎች) ከፍተኛ የኢነርጂ ተጠቃሚ አካላት የኢነርጂ አጠቃቀም ዕቅድና መርሃ ግብር እንዲያወጡ ሊያደርግና አፈጻጸማቸውን ሪፖርት እንዲያደርጉለት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ የሚቀርብለትን የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ከመርሃ-ግብሩ አንፃር የመገምገምና ውጤቱን ለሚመለከታቸው ተቆጣጣሪ አካላት ሊያሳውቅ ይገባል፡፡

65. ይሁን እንጂ ከፍተኛ የኢነርጂ ተጠቃሚ አካላት የኢነርጅ አጠቃቀም የፈቃደኝነት ስምምነት ያልፈረሙ በመሆኑ የኢነርጂ አጠቃቀም ዕቅድና መርሃ-ግብር እንደማያዘጋጁ እንዲሁም ባለሥልጣን መ/ቤቱም እንዲያዘጋጁ እንደማያደርግ እና የመገምገምና ውጤቱን የማሳወቅ (ለውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር፣ ለህዝብ ተወካዮች ለተፈጥሮ ሀብት ልማትና አከባቢ ጥበቃ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ወ.ዘ.ተ) ስራም እንዳልሰራ በኦዲት ወቅት ከተሰበሰበው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

66. በናሙና ተመርጠው ከታዩት ተቋማት፡

- አቃቂ ብረታ ብረት ፋብሪካ፣ አላርት ሆስፒታል፣ ግዮን ሆቴል፣ ጁፒተር ሆቴል፣ ደብረ ብርሃን ብርድልብስ ፋብሪካ፣ ሞሀ ለስላሳ መጠጦች ኢንድስትሪ፣ ከአራራት ሆቴል፣ ሂልተን ሆቴል፣ አይካ አዲስ ቴክስታይል፣ ቅዱስ ገብሪኤል ሆስፒታል እና ቅድስ ጳውሎስ ሆስፒታል የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው የኢነርጂ አጠቃቀም እቅድ እንደማያቅዱ እና ግንዛቤውም የሌላቸው መሆኑ፣ ስለኢነርጂ ከባለስልጣን መ/ቤቱ ኢነርጂን አስመልክቶ የሚደረግላቸው የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራና የውይይት መድረክ እንዳልተዘጋጀ እና የኢነርጂ አጠቃቀምን አስመልክቶ ለባለስልጣን መ/ቤቱ የሚደረግ ሪፖርት እንደሌለ እና ሪፖርት አድርገው እንደማያውቁ እንዲሁም
- ኢስት አፍሪካ ቦትሊንግ ፋብሪካ፣ ሆራይዘን አዲስ ጎማ አክስትዮን ማህበር፣ ለሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካ፣ ሸራተን አዲስ ሆቴል፣ ቢ.ጂ.አይ ኢትዮጵያ እና ኮምቦልቻ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ የስራ ኃላፊዎች በራሳቸው ተነሳሽነት ያዘጋጁት የኢነርጂ አጠቃቀም ዕቅድ እንዳላቸውና ለኢነርጂ ባለስልጣን የሚልኩት ሪፖርት ግን እንደሌለ፣

67. በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡ ባለስልጣን መ/ቤቱም የሚያዘጋጃቸው ኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ አሰራር የትንታኔ ሪፖርት ለባለድርሻ አካላት ሪፖርት እንደማያደርግ የባለስልጣን መ/ቤቱ የ2007 ዓ.ም በተደረገው የውስጥ ኦዲት ሪፖርት ከተገኘው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

68. ስለሁኔታው የባለስልጣን መ/ቤት የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው ከፍተኛ የኢነርጂ ተጠቃሚ አካላት የኢነርጂ አጠቃቀም ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ከመርሃ-ግብሩ አንፃር የመገምገምና ውጤቱን የማሳወቅ ስራ ያልተሰራበት ምክንያት የኢነርጂ ማኔጅመንት ዩኒት በየዘርፉ ልተዘጋጀና ደንቡ ባለመፅደቁ መሆኑንን ለቀረበላቸው መጠይቅ እና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡ ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ አሁን ባለው ህግ ዕቅድና መርሃ ግብር ተቋማቱ በማዘጋጀት አንዲሰሩና አፈጻጸሙን ሪፖርቱን በማድረግ መከታተል ይቻል ስለነበር የሰጡትን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

69. ከፍተኛ የኢነርጂ ተጠቃሚ አካላትን የኢነርጂ አጠቃቀም ዕቅድና መርሃ ግብር እንዲያወጡ በማድረግ እና የአፈፃፀም ሪፖርት እንዲደርሰው በማድረግ ከመርሃ-ግብሩ አንፃር የመገምገምና ውጤቱን የማሳወቅ ስራ አለመሰራቱ የአገሪቱን የኢነርጂ አተቃቀም ሂደት ምን እንደሚመስል ለማወቅ ከማቸገሩም አንጻር ተገቢውን ድጋፍ ለማድረግንም አጋጃች ያደርገዋል፡፤

## የኢነርጂ ፈንድ ተቋቁሞ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤

70. የኢነርጂ ፈንድ በአዋጅ ቁጥር 810/2006 አንቀጽ 23 መሰረት ሊቋቋምና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ በኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ዘርፍ ለሚሳተፉ የኢነርጂ ተጠቃሚ ተቋማት የቴክኒክና የፋይናንስ ድጋፍ ሊደረግ ይገባል፡፡

71. ይሁን እንጂ የኢነርጂ ፈንድ ባለመቋቋሙ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ዘርፍ ለሚሳተፉ ተቋማት የቴክኒክና የፋይናንስ ድጋፍ አለመደረጉን በኦዲት ወቅት ከተሰበሰበው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

72. በናሙና ተመርጠው ከታዩት ከፍተኛ የኢነርጂ ተጠቃሚዎች ኮምቦልቻ ጨርቃጨርቅ፣ ሙገር ሲሚንቶ፣ ደብረብርሃን ብርድልብስ፣ አይካ አዲስ ጨርቃጨርቅ፣ ሆራይዘን አዲስ ጎማ፣ ለአቃቂ ብረታ ብረት፣ ሞሀ ለስላሳ መጠጦች፣ ለቢ.ጂ.አይ ኢትዮጵያ እና ኢስት አፍሪካ ቦትሊንግ ፋብሪካዎች፣ አላርት፣ ጥቁር አንበሳ፣ ፌዴራል ፖሊስ፣ ቅድስ ጳውሎስ እና ቅዱስ ገብሪኤል ሆስፒታሎች እና ሂልተን፣ ሸራተን አዲስ፣ ጁፒተር ኢንተርናሽናል፣ አራራት እና ግዮን ሆቴሎች የሰራ ኃላፊዎች ተጠይቀው የተደረገላቸው የቴክኒክ እና የፋይናንስ ድጋፍ እንደሌለ በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ አስተያየታቸውን ገልጸዋል፡፡

73. ስለሁኔታው የባለስልጣን መ/ቤቱ የስራ ኃላፊ ተጠይቀው የፋይናንስ ድጋፍ ለሚፈልጉ ተግባራዊ ለማድረግ ዝርዝር አፈጻጸም ሁኔታ ይጸድቃል ተብሎ በሚጠበቀው የኢነርጂ አዋጅ ማስፈጸሚያ ደንብ ላይ የሚገለጽ ይሆናል በማለት በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ አስተያየታቸውን ገልፀዋል፡፡

74. በመሆኑም በኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ዘርፍ ለሚሳተፉ ተቋማት የቴክኒክና የፋይናንስ ድጋፍ ባለመኖሩ ከፍተኛ ኃይል ተጠቃሚዎች በኢነርጂ ዘርፍ ዙሪያ ያለው የቴክኒክ ግንዛቤ እጥረት እንዲኖር እና ኃይል አባካኝ የሆኑ የኢነርጂ መጠቀሚ ቴክኖሎጂዎች በኃይል ቆጣቢ ለመተካት የመግዛት አቅም የሌላቸው ተቋማት

የፋይናንስ ድጋፍ እንዳይኖራቸው ክፍተት ከመፍጠሩም በላይ ላላስፈላጊ ወጪ እንዲዳረጉ እና ተቋሞች መቆጠብ የሚገባቸውን የኢነርጂ መጠን እንዳይቆጠብ አድርገዓል፡፡

## ከፍተኛ የኢነርጂ ተጠቃሚዎች የኢነርጂ ኦዲት ግኝት በተገኘባቸው ላይ የማስተካከያ እርምጃ መወሰዱን በተመለከተ፤

75. በተመረጡና ከፍተኛ የኢነርጂ አጠቃቀም ደረጃ ባላቸው ተቋማት ላይ የኢነርጂ ኦዲት ሊደረግ እና ግብረ መልስ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ በኢነርጂ ኦዲቱ ወቅት ግኝት የተገኘባቸው ተቋማት የማስተካከያ እርምጃ ሊወስዱ ይገባል፡፡ ባለሥልጣኑም እርምጃው ስለመወሰዱ ክትትል ሊያደረግ ይገባል፡፡

76. ይሁን እንጂ ከፍተኛ የኢነርጂ ተጠቃሚ ተቋማት ላይ የኢነርጂ ኦዲት አልፎ አልፎ እንደሚደረግ በኦዲት ወቅት ከተሰበሰበው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በናሙና ተመርጠው ከታዩት ከፍተኛ ኢነርጂ ተጠቃሚዎች ውስጥ ሆራይዘን አዲስ ጎማ እና ሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካዎች በባለስልጣን መ/ቤቱ የኢነርጂ ኦዲት ተደርገው የኦዲት ሪፖርቱ እንደተላከላቸው እና በተሰጠውን ማሻሻል ሃሳብ መሰረት ለመተግበር ጥረት እየተደረገ እንደሆነና ግብረ መልስም እንዳልተሰጣቸው ሌሎቹ ግን ኦዲት ተደርገው እንደማያውቁ የየድርጅቶቹ የስራ ኃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ገልጸዋል፡፡

77. ስለሁኔታው የባለስልጣን መ/ቤት የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው ኦዲት የተደረጉ ከፍተኛ የኢነርጂ ተጠቃሚዎች ቢኖሩም በሚፈለገው መጠን እየተሰራ እንዳልሆነና ኦዲት በተደረጉ ኢንዳስትሪዎች ላይ የመልሶ ማረጋገጥ ስራ እየተሰራ መሆኑንና የኢነርጂ አዋጅ ማስፈጸሚያ ደንቡ ሳይቀፀድቅ የሚሰሩት የኢነርጂ ኦዲት ስራዎች ማስፈፀሚያ መሳሪያ ስሌላቸው አዋጭነቱ ላይ በመተማመን እንደሚሰራ እና የኦዲት ውጤቱን ትግበራዊ እንዲያደርጉ የሚያስገድድ ደንብ አለመኖሩ እና ኢንዱስትሪዎቹ ተግባራዊ ለማድረግ ፍቃደኛ የሆኑ ቢሆንም ኃይል ቆጣቢ፣ ብቃት ያላቸው እና ማገልገል የሚገባቸውን ጊዜ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ የኢነርጂ መጠቀሚያ ቴክኖሎጂ የዕቃዎች አቅርቦት በበቂ ሁኔታ አለመገኘት እንዳይተገብሩት እንቅፋት እንደሆነባቸው ለቀረበላቸው መጠይቅና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ ላይ ገልፀዋል፡፡

78. ከፍተኛ የኢነርጂ ተጠቃሚ ተቋማት ላይ መርሃ ግብር ወጥቶ የኢነርጂ ኦዲት አለመደረጉ እና በተደረጉትም ላይ በተገኘባቸው ላይ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ አለመደረጉ የኢነርጂ ቁጠባና ብቃት ለማምጣት ለሚደረገው ጥረት ከኦዲቱ የሚገኝ ድጋፍ ያሳጣዋል፡፡

**ከፍተኛ የኢነርጂ ተጠቃሚ አካላት የኢነርጂ አመራር የስራ ክፍል (Energy Management Unit) ማቋቋማቸውን በተመለከተ፤**

79. ባለስልጣን መ/ቤቱ በኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ የኢነርጂ አጠቃቀምን አስመልክቶ ከከፍተኛ የኢነርጂ ተጠቃሚ አካላት የኢነርጂ አመራር የስራ ክፍል (Energy Management Unit) ሊያቋቁሙ ይገባል፡፤ ድርጅቶቹም ይህ ክፍል እንዲያቋቁሙ ለማድረግ ባለሥልጣን መ/ቤቱ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ሊሰራ ይገባል።

80. ይሁን እንጂ ከፍተኛ የኢነርጂ ተጠቃሚ አካላት የኢነርጂ አመራር የስራ ክፍል (Energy Management Unit) በአዋጅ ቁጥር 810/2006 አንቀጽ 19 መሰረት እንዳላቋቋሙ፣ ባለሥልጣን መ/ቤቱም ድርጅቶቹ ይህን ክፍል እንዲያቋቁሙ ለማድረግ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ እንዳልሰራ በኦዲት ወቅት ከተሰበሰበው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በናሙና ተመርጠው የታዩት ከፍተኛ ኢነርጂ ተጠቃሚዎች ተቋማት የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በድርጅታቸው ውስጥ የኢነርጂ አመራር የስራ ክፍል (Energy Management Unit) እንዳላቋቋሙ እና አስፈላጊነቱም ላይ ግንዛቤ እንደሌላቸው በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

81. ስለሁኔታው የባለስልጣን መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው የአፈፃፀሙ ሁኔታ ይፀድቃል ተብሎ በሚጠበቀው ደንብ ውስጥ የሚገለጽ ሲሆን በደንቡ አግባብ መሰረት ሲፀድቅ የሚሰራ መሆኑን በቀረበላቸው መጠይቅ እና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ ላይ ገልፀዋል፡፡

82. ከፍተኛ የኢነርጂ ተጠቃሚ አካላት የኢነርጂ አመራር የስራ ክፍል (ENERGY MANAGEMENT UNIT) አለማቋቋማቸው የኢነርጂ ብክነት ለመቀነስ የሚደረገው ጥረት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡

**ከኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ጋር ተዛማጅ የሆኑ መረጃዎችን አሰባሰብና ልውውጥን በተመለከተ፤**

83. ባለስልጣን መ/ቤቱ ከኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ጋር ተዛማጅ የሆኑ መረጃዎችን ሊሰበስብ፤ ሊተነትን፤ ሊያደራጅ ይገባል፡፡ መረጃዎቹንም ለሚፈልጉት እና ለተቆጣጣሪ አካላት በተለያዩ መንገዶች (በመረጃ መረብ፣ በኤሌክትሮኒክ ሚዲያዎች፣ በብሮሸሮች፣ ወዘተ) ሊያሰራጭ ይገባል፡፡

84. ይሁን እንጂ ከኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ጋር ተዛማጅ የሆኑ መረጃዎችን በመሰበሰብ፤ በመተንትን እና በማደራጀት ለሚመለከተው አካል እንዳላሰራጨ ታውቋል፡፡

85. ስለጉዳዩ የውሃ፣ መስኖ እና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው እንደ ሀገር ኤሌትሪክን አስመልክቶ ያለው የመረጃ አያያዝ ችግር ለኤሌትሪክ ብክነት መንስኤ እንደሚሆንና ለአብነትም በትላልቅ ሃይል ተጠቃሚ እንዳስትሪዎች የኤሌትሪክ ፍጆታቸው ዳታ በአግባቡ ተይዞ እንደማይገኝ እና ይህን የመረጃ አያያዝ ችግር መቆጣጠርና መከታተል የሚጠበቅበት የኢትዮጵያ ባለስልጣን መ/ቤት ተግባር መሆኑን በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

86. ስለጉዳዩ የባለሥልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው ከኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ጋር ተዛማጅ የሆኑ መረጃዎችን የማሰባሰብ፣ የመተንተን፣ የማደራጀት እና ለሚመለከተው አካል የማሰራጨት ሰራ ያልተሰራ ቢሆንም ሙከራዎች ግን እንዳሉ በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ አስተያየታቸውን ገልፀዋል፡፡

87. ከኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ጋር ተዛማጅ የሆኑ መረጃዎችን በመሰበሰብ፤ በመተንትን እና በማደራጀት ለተጠቃሚዎችና ለውሳኔ ሰጭ አካላት አለመሰራጨቱ የኢነርጂ መረጃዎች በተጠናከረ መልክ ተደራጅቶ እንዳይቀመጥ እና እንደአስፈላጊነቱ የኢነርጂ መረጃ ፈላጊዎች እንዳይጠቀሙት ከማድረጉም በላይ ኢነርጂን አስመልክቶ ለሚደረጉ የፖሊሲና ስትራቴጂ ውሳኔዎች አሉታዊ ተጽዕኖ ይፈጥራል፡፡

## የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ሰርቶ ማሳያ በተመለከተ፤

88. ባለስልጣን መ/ቤቱ የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ሰርቶ ማሳያ ሊያዘጋጅ፣ ሊያስፋፋና ሌሎችም ይህንኑ ተግባራዊ እንዲያደርጉ ሊያስተባብር ይገባል፡፡

89. ይሁን እንጂ የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ሰርቶ ማሳያ ባለስልጣን መ/ቤቱ እንዳልተሰራ እና ለሰርቶ ማሳያ የተገዙ ዕቃዎችም ለክልሎች እንደተላኩ እንዲሁም ክልሎችም በምን ደረጃ እንዳደረሱት መረጃው እንደሌለ በኦዲቱ ወቅት ከተሰበሰበው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ስለጉዳዩ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ዳይሬክተር የኢነርጂ አዋጅ ማስፈጸሚያ ደንብ ባለመውጣቱ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ሰርቶ ማሳያ አለመሰራቱን በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም የኢነርጂ ሰርቶ ማሳያ እንዳልተሰራ በባለስልጣን መ/ቤቱ ከተከለሱት መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

90. ስለሁኔታው የባለስልጣን መ/ቤት የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ሰርቶ ማሳያ በባለሥልጣኑ አለመሰራቱን ነገር ግን ከክልል ቢሮዎች ጋር በመተባበር ለስድስት ክልሎች የሰርቶ ማሳያ ጣቢያ እንዲቋቋም በፕሮጀክት የተደገፈ የዕቃዎች ድጋፍ እንዳደረጉ በቀረበላቸው መጠይቅና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ ላይ ገልጸዋል፡፡ ሆኖም ግን ክልሎቹም የሰርቶ ማሳያ ጣቢያ ያቋቋሙ ስለመሆናቸው አልገለጹም፡፡

91. በመሆኑም የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ሰርቶ ማሳያ ባለመሰራቱ ኢነርጂ ተጠቃሚ አካላት የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ግንዛቤ እንዳይኖራቸው እና ኃይል ቆጣቢና ብቃት ያላቸው የኤሌትሪክ ዕቃዎችን እንዳይጠቀሙ ክፍተት ፈጥሯል፡፡

## በባለስልጣን መ/ቤቱ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባን በሚመለከት የሚነሱ ቅሬታዎች የአፈታት ስርዓት መኖሩንና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤

92. በባለስልጣን መ/ቤቱ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባን በሚመለከት የሚነሱ ቅሬታዎች የአፈታት ስርዓት ሊኖርና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

93. በኦዲት ወቅት ከከፍተኛ የኃይል ተጠቃሚዎች የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ዙሪያ ለሚያነሷቸው ቅረታዎች የአፈታት ሥርዓት በባለስልጣኑ መ/ቤቱ የሌለ መሆኑን ከተሰበሰበው ማስረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

94. በናሙና ተመርጠው የታዩት ከፍተኛ ኢነርጂ ተጠቃሚ ተቋማት በባለስልጣን መ/ቤቱ በተሰጣቸው አስተያየት መሰረት የሀይል ብክነት መቆጣጠሪያ ፓዎር ፋክተር ኮሬክተር ለማስገጠም ክፍያ የፈፀሙ ቢሆንም እንዳልተገጠመላቸው፣ ብቃት

ያላቸውና ሀይል ቆጣቢ የሆኑ ማሽነሪች፣ መሳሪዎች፣ ጀነሬተሮች እና አምፓሎች በገበያ ላይ በበቂ ሁኔታ አለመኖር እና ያሉትም ጥራት የሌላቸው መሆኑ፣ በተደጋጋሚ የመብራት መቆራረጥ ችግር በምርታቸውና አገልግሎታቸው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ በመፍጠር ለምርት ብክነት፣ አገልግሎት በማስተጓጎል እና ለተጨማሪ ወጪ እንደተዳረጉ፣ የኤሌክትሪክ ካርዶች በወቅቱ አለመቅረብ፣ በኤሌክትሪክ ምክንያት ማሽኖች መቃጠል እና ሌሎችም በርካታ ቅሬታዎች መኖሩን የተቋሞቹ የስራ ኃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ገልጸዋል፡፡

95. ስለጉዳዩ የመስሪያ ቤቱ ሀላፊዎች ተጠይቀው አስተያየት አልሰጡም፡፡

96. የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ዙሪያ ለሚያነሷቸው ቅሬታዎች የአፈታት ሥርዓት ባለመኖሩ ከፍተኛ ሀይል ተጠቃሚ ተቋማት ለምርት ብክነት፣ አገልግሎት በማስተጓጎል እና ለተጨማሪ ወጪ ተዳርገዋል፡፡

## ክፍል ሶስት

## መደምደሚያ

97. በሁለተኛ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዘመን በከፍተኛ ወጪ እየተገነቡ ካሉት ሜጋ ፕሮጀክቶች የኢነርጂ ግንባታ ዋነኛ በመሆኑ የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለስልጣን የኢነርጂ ቁጠባና ብቃት አፈጻጸምን ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መንገድ እየሰራ መሆኑ ሲገመገም የሚከተሉት ዋና ዋና ግድፈቶች ተገኝተዋል፡-

- የኢነርጂ ብቃትና ቁጣባን የሚመለከቱ ደንብና መመሪያዎች ያልጸደቀ መሆኑ፣
- ባለስልጣን መ/ቤቱ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ መፈተሻ ስርዓት ያልተዘረጋ እና የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ መፈተሻ ላብራቶሪዎችም ያልተቋቋሙ መሆኑ፣
- የኢነርጂ መጠቀሚያና የኤሌክትሪክ አገልግሎት የሚውሉ ቴክኖሎጂዎች የአጠቃቀም ደረጃ (Standard) ያልወጣ መሆኑን፣
- በባለስልጣን መ/ቤቱ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ፕሮግራም አለመዘጋጀቱ፣
- የኢነርጂ ብቃት ደረጃዎች ኮድ፣ የኢነርጂ ብቃት ማረጋገጫ ተለጣፊ ኮድ፣ የኢነርጂ ኦዲት ኮድ ያልወጣ መሆኑ፣
- ከፍተኛ ኢነርጂ ተጠቃሚዎች ጋር የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባን የሚያበረታታ የተሻለ የኢነርጂ አጠቃቀም ያላቸው ተቋማት የፈቃደኝነት ስምምነት እንዲሁም ኃይል አባካኝ ወይም የኃይል ብክነት የሚታይባቸው ተቋማት የአስገዳጅነት ስምምነቶች የማይደረጉ መሆኑ፣
- ኤሌክትሪክ በማመንጨት፣ በማሰተላለፍ፣ በማከፋፈል እና በመሸጥ ስራ ላይ ለተሰማሩ የፈቃድ የመስጠት ስራ እየተሰራ አለመሆኑ እንዲሁም ለኢነርጂ ኦዲተሮችንና የኢነርጂ ኦዲት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች (ኩባንያዎች) የፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ ስላልተዘጋጀ ፈቃድ የመሰጠቱ ስራ የማይሰራ መሆኑ፣
- ከፍተኛ ኢነርጂ ተጠቃሚዎች የኢነርጂ አጠቃቀማቸው አስመልክቶ ባለስልጣኑ የቁጥጥር እና የክትትል ስራ የማይሰራ መሆኑ፣
- ኃይል ቆጣቢ የሆኑ መሳሪያዎችን የኢነርጂ አጠቃቀም ደረጃ አለመኖሩ፣

- ❖ የኢነርጂ መጠቀሚያ ቴክኖሎጂዎችን ለመለየትና አጠቃቀማቸውን ማወቅ የሚያስችል የመነሻ ጥናት (Baseline) አለመከናወኑ፣
- ❖ የሀገሪቱ የኢነርጂ ፍላጎት፣ ጥቅም ላይ የዋለ እና ያልዋለ የኢነርጂ መጠን በባለስልጣን መ/ቤቱ የማይታወቅ መሆኑ፣
- ❖ ኢነርጂ ቆጣቢ የሆኑ የኢነርጂ መጠቀሚያ ቴክኖሎጂዎችን ለገበያ ከመቅረባቸው በፊት የሚያሟሉት ደረጃ ታውቆ በየመሣሪያዎቹና ዕቃዎቹ ላይ ደረጃቸውን የሚገልጽ ተለጣፊ ምልክት እንዲለጥፉ የሚያረጋግጥ ፈቃድ ለአቅራቢዎች ያልተሰጠ መሆኑ፣
- ❖ የኢነርጂ ፈንድ በአዋጅ ቁጥር 810/2006 አንቀጽ 23 መሰረት አለመቋቋሙ፣
- ❖ ከፍተኛ የኢነርጂ ተጠቃሚ አካላት የኢነርጂ አመራር የስራ ክፍል (Energy Management Unit) እንዲያቋቁሙ አለመደረጉ፣
- ❖ ከኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ጋር ተዛማጅ የሆኑ መረጃዎችን በመሰበስብ፤ በመተንተን እና በማደራጀት ለሚመለከተው አካል እለመሰራጨቱ፣
- ❖ የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ሰርቶ ማሳያ ባለስልጣን መ/ቤቱ ያልተሰራ መሆኑ፣
- ❖ ከፍተኛ የኢነርጂ ተጠቃሚ ተቋማት ላይ የሚከናወነው የኢነርጂ ኦዲት ግኝት መሰረት የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱ የማይደረግ መሆኑ፣
- ❖ ከፍተኛ የኃይል ተጠቃሚዎች የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ዙሪያ ለሚያነሷቸው ቅሬታዎች የአፈታት ሥርዓት በባለስልጣኑ መ/ቤቱ የሌለ መሆኑን፣

98. ስለሆነም በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን ድክመቶች እና ችግሮች ለማስወገድ ወይንም ለማቃለል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል አቅርበናል፡፡

## ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሀሳቦች

99. ባለስልጣን መ/ቤቱ የኢነርጂ ቁጠባ እና ብቃት አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ እንዲሆን በሀገሪቱ የተሻለ የኢነርጂ አጠቃቀም እንዲኖርና የኢነርጂ ቁጠባ እና ብቃት ውጤታማ እንዲሆን ዘመናዊና ሃይል ቆጣቢ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን የሚጠቀም ማህበረሰብ እንዲኖር ግንዛቤ እንዲፈጠር ለማስቻል ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ በመስራት ችግሮችን ለመፍታት ያስችላሉ ያልናቸውን የሚከተሉትን የማሻሻያ ሀሳቦች አቅርበናል፡-

- ባለስልጣን መ/ቤቱ የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ደንብና መመሪያዎች (Energy Efficiency and Conservation Rule and Regulation) በአስቸኳይ በሚመለከተው አካል አጸድቆ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ኃይል ቆጣቢ እና ብቃት የሌላቸው ኢነርጂ ምርቶች ገበያ ላይ እንዳይሰራጩ እና ተጠቃሚዎች ለስተት እንዳይዳረጉ ባለስልጣን መ/ቤቱ የኢነርጂ ብቃት እና ቁጣባ የመፈተሻ ስርዓት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ በማድረግ የመፈተሻ ላብራቶሪዎችን በማቋቋም ወደ ተግባር ሊገባ ይገባል፡፡
- ለኢነርጂ መጠቀሚያና ለኤሌክትሪክ አገልግሎት የሚውሉ ቴክኖሎጂዎች ኃይል ቆጣቢ እና ብቃት ያላቸው መሆኑን የሚለይበት የአጠቃቀም ደረጃ (Standard) አውጥቶ በሚመለከተው አካል በማጸደቅ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል::
- በባለስልጣን መ/ቤቱ በስራ ላይ የዋለውን የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ፕሮግራም በማዘጋጀት ከባለድሻ አካካለት ጋር ግባት በ፣ሰባሰብ እና በሚመለከተው አካል በማጸደቅ ተግባራዊ ሊያደርግ እና በየጊዜው አፈጻጸሙን በመገምገም ፕግራሙ ያስገኘው ውጤት ሊለካ ይገባል።
- ባለስልጣን መ/ቤቱ የኢነርጂ ብቃት ደረጃዎች ኮድ፣ የኢነርጂ ብቃት ማረጋገጫ ተለጣፊ ኮድ፣ የኢነርጂ ኦዲት ኮድ በማውጣት ኃይል ቆጣቢ እና ብቃት ያላቸውን የኢነርጂ መጠቀሚያ ቴክኖሎጂዎች ብቻ አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

- ባለስልጣኑ በብሄራዊ ደረጃ ከከፍተኛ ኢነርጂ ተጠቃሚዎች ጋር በአዋጁ መሰረት የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባን የሚያበረታታ የተሻለ የኢነርጂ አጠቃቀም ያላቸው ተቋማት የፈቃደኝነት እንዲሁም የኃይል ብክነት የሚታይባቸው ተቋማት የአስገዳጅነት ስምምነቶች ሊኖርና ስምምነቱን በማይፈፅሙት ላይ እርምጃ የሚወሰድበት አሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ባለስልጣን መ/ቤቱ በየዘርፉ (በኢንዱስትሪዎች፣ ሆቴሎች፣ ሆስፒታሎች እና ሌሎች) ከፍተኛ የኢነርጂ ተጠቃሚ አካላት የኢነርጂ አጠቃቀም ዕቅድ፣ የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት እና የእቅድ መርሃ-ግብር እንዲያዘጋጁ በማድረግ ለባለስልጣን መ/ቤቱ ሪፖርት እንዲያደርጉ እና ባለስልጣን መ/ቤቱ የግምገማ ስራ ሊሰራና ውጤቱን ለሚመለከተው አካል ሊያሳውቅ ይገባል፡፡
- ኢነርጂ ተጠቃሚ ተቋማት አማራጭ የኢነርጂ አገልግሎት አቅራቢዎች እንዲኖራቸው ኤሌክትሪክ በማመንጨት፣ በማስተላለፍ፣ በማከፋፈል እና በመሸጥ ስራ ላይ ለተሰማሩ እንዲሁም ብቃት ያላቸውና ኃይል ቆጣቢ የሆኑ የኢነርጂ መጠቀሚያ ቴክኖሎጂ እቃዎች እየተጠቀሙ እንደሆኑ ለመከታተልና ለመቆጣጠር ለኢነርጂ ኦዲተሮች እና ለኢነርጂ ኦዲት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች (ኩባንያዎች) የፈቃድ አሰጣጥ የአሰራር ስርዓት ሊኖርና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ከፍተኛ ኢነርጂ ተጠቃሚዎች የኢነርጂ አጠቃቀማቸው የተሻለ እንዲሆን ብቃት ያላቸው እና ኃይል ቆጣቢ የሆኑ የኢነርጂ ቴክኖሎጂ እቃዎችን እንዲጠቀሙ እና ኃይል አባካኝ የሆኑት መሳሪያዎች አገልግሎት ላይ አለመዋላቸውን ባለስልጣኑ የቁጥጥር እና የክትትል ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡
- ብቃት ያላቸው እና ኃይል ቆጣቢ የሆኑ የኢነርጂ መሳሪያዎችን ለይቶ መጠቀም የሚያስችል የኢነርጂ አጠቃቀም ደረጃ እና ጋይድላይን ተዘጋጅቶና ተግባራዊ ሊያደርግ እና ኢነርጂ አጠቃቀምን ማወቅ የሚያስችል የመነሻ ጥናት (Baseline) በማካሄድ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡
- የሀገሪቱ የኢነርጂ ፍላጎት፣ ጥቅም ላይ የዋለ እና ያልዋለ የኢነርጂ መጠን በባለስልጣን መ/ቤቱ ሊታወቅ እና ተመዝግበው ሊያዙ ይገባል፡፡ መረጃዎቹንም በመተንተን ውጤቱን ለስትራቴጂክ እና ለፖሊሲ ውሳኔ ግብዓት እንዲሆን ለሚመለከታቸው አካላት ሊያቀርብ ይገባል፡፡

- ኃይል ቆጣቢ የሆኑ እና ብቃት ያላቸው የኢነርጂ መጠቀሚያ ቴክኖሎጂዎች ለገበያ ከመቅረባቸው በፊት የሚያሟሉት ደረጃ ታውቆ በየመሳሪያዎቹና ዕቃዎቹ ላይ ደረጃቸውን የሚገልጽ የተለጣፊ ምልክት እንዲለጠፍ ለአቅራቢዎች የሚያረጋግጥ ፈቃድ ሊሰጥ፣ ተጠቃሚው ህብረተሰብም በቀላሉ እንዲያውቃቸው ለማድረግ የማስተዋወቅ ሥራ ሊሰራ ይገባል፡፡
- ከፍተኛ ኢነርጂ ተጠቃሚዎች ኃይል ቆጣቢ እና ብቃት ያላቸው ቴክኖሎጂ እቃዎች ብቻ አገልግሎት ላይ መዋሉን ለመከታተል እና ለመቆጣጠር የኢነርጂ ኦዲት ስራ በሚፈለገው ደረጃ ሊሰራ እና ግብረ መልስ ሊሰጥ እንዲሁም ጉልህ ግኝት በተገኘባቸው ላይ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ክትትል እና ቁጥጥር ሊያደረግ ይገባል፡፡
- ኢነርጂ ተጠቃሚ ተቋማት ኃይል አባካኝ የሆኑ እና ብቃት የሌላቸው የኢነርጂ መጠቀሚ ቴክኖሎጂዎች በኃይል ቆጣቢና ብቃት ባላቸው ለመተካት እንዲችሉ የፋይናንስ ድጋፍ ለማድረግ በአዋጁ መሰረት የኢነርጂ ፈንድ ሊያቋቁም እና ተግባራዊ ሊያደረግ ይገባል፡፡
- ባለስልጣን መ/ቤቱ በኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ የኢነርጂ አጠቃቀምን አስመልክቶ ከከፍተኛ የኢነርጂ ተጠቃሚ አካላት የኢነርጂ አመራር የስራ ክፍል (Energy Management Unit) እንዲያቋቁሙ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ በስፋት ሊሰራ ይገባል።
- ባለስልጣን መ/ቤቱ ከኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በመተንተን እና በማደራጀት ለሚመለከተው አካል ሊያሰራጭ ሊያሰራጭ እንዲሁም የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ አስፈላጊነት ዙርያ ለኢነርጂ ተጠቃሚዎችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ተደራሽ እና ተደማጭ በሆኑ ማስታወቅያ መንገዶች የግንዛቤ መስጫ ስራዎች ሊሰሩ ይገባል፡፡
- ባለስልጣን መ/ቤቱ ህብረተሰቡ ስለኢነርጂ ግንዛቤያቸውን ለማሳደግ በቀላሉ ሊገነዘቡ እና ሊማሩት እንዲችሉ የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ሰርቶ ማሳያ ሊኖር እና ሊስፋፋ እንዲሁም ሌሎችም ይህንኑ ተግባራዊ እንዲያደርጉ ሊያስተባብር ይገባል፡፡

- ባለስልጣን መ/ቤቱ ከፍተኛ የኢነርጂ ተጠቃሚዎች ለሚያነሷቸው ቅሬታዎች ምንጮቹን በመለየት የሚፈቱበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

100. በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለስልጣን መ/ቤት እና በናሙና የታዩት ተቋማት የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በኦዲቱ ወቅት ስላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

Office of the Federal Auditor General

## አባሪ 1


## የኦዲት መመዘኛ መስፈርት

| የኦዲት ጭብጥ (Audit Issues) | የኦዲት የመመዘና መስፈርቶች (Evaluative criteria) |
|---|---|
| 1. **የኢነርጂ ብቃት (Energy Efficiency) ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ መሆኑን መገምገም ፤** | 1. ባለስልጣን መ/ቤቱ የኢነርጂ ብቃት ደንብና መመሪያዎች (Energy Efficiency Rule And Regulation) ሊያዘጋጅና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 2. ባለስልጣን መ/ቤቱ የረጅም፣ የመካከለኛ እና የአጭር ጊዜ የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ስትራቴጂ የሚመለከታቸው አካላትን በማሳተፍ ሊያዘጋጅና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 3. ባለስልጣን መ/ቤቱ የተዘጋጁትን የረጅም፣ የመካከለኛ እና የአጭር ጊዜ የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ስትራቴጂ አፈፃፀምን በየወቅቱ ሊገመግም ይገባል፡፡ |
| | 4. ባለስልጣን መ/ቤቱ የኢነርጂ ብቃት የመፈተሻ ስርዓት ሊያወጣና ሊተገብር ይገባል፡፡ |
| | 5. ባለስልጣን መ/ቤቱ የኢነርጂ ብቃት መፈተሻ ላብራቶሪዎችን ሊያቋቁም ይገባል፡፡ |
| | 6. ለኢነርጂ መጠቀሚያና ለኤሌክትሪክ አገልግሎት የሚውሉ ቴክኖሎጂዎች የአጠቃቀም ደረጃ (Standard) ሊያወጣና በሚመለከተው አካል በማጸደቅ ተግባራዊ መሆኑን ሊቆጣጠር ይገባል:: |
| | 7. ባለስልጣን መ/ቤቱ በስራ ላይ የዋለውን የኢነርጂ ብቃት ፕሮግራም አፈጻጸም ያስገኘውን ተጽዕኖ መለካት የሚያስችል የግምገማ ጥናት (Impact Assesment) ሊደረግ ይገባል። |
| | 8. ባለስልጣን መ/ቤቱ፤ የኢነርጂ ብቃት ደረጃዎች ኮድ፤ የኢነርጂ ብቃት ማረጋገጫ ተለጣፊ ኮድ፤ የኢነርጂ ኦዲት ኮድ ሊያወጣና አፈፃፀሙንም ሊከታተል ይገባል፡፡ |
| | 9. ባለስልጣኑ በብሄራዊ ደረጃ ከፍተኛ ኢነርጂ ተጠቃሚዎች የኢነርጂ ብቃትን የሚያበረታታ የፈቃደኝነት ስምምነት ሊኖርና ተግባራዊ ሊደረግ እንዲሁም ስምምነቱን በማይፈፅሙት ላይ እርምጃ የሚወሰድበት ስርዓት ሊኖር ይገባል፡፡ |
| | 10. ኤሌክትሪክ በማማንጨት፣ በማሰተላለፍ፣ በማከፋፈልና በመሸጥ ስራ ላይ የተሰማሩ የፈቃድ አሰጣጥ የአሰራር ስርአት ሊኖር እና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 11. የኢነርጂ ኦዲተሮችንና የኢነርጂ ኦዲት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች (ኩባንያዎች) የፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ ሊዘጋጅ እና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 12. ከፍተኛ ኢነርጂ ተጠቃሚዎች የኢነርጂ አጠቃቀማቸው የተሻለ እንዲሆን የኢነርጂ አጠቃቀም ብቃት ያላቸውን የኢነርጂ ቴክኖሎጂዎችን እንዲጠቀሙ ባለስልጣኑ የቁጥጥር እና የክትትል ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡ |

| የኦዲት ጭብጥ (Audit Issues) | የኦዲት የመመዘና መስፈርቶች (Evaluative criteria) |
|---|---|
| | 13. ባለስልጣን መ/ቤቱ የኢነርጂ ኦዲት የፈቃድ አሰጣጥ መስፈርት ሊያዘጋጅ እና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 14. ባለስልጣን መ/ቤቱ በኤሌክትሪክ ስራ ለተሰማሩ ግለሰቦች የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሊሰጥና በየዓመቱ እንዲታደስ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| 2. **የኢነርጂ ቁጠባ (Energy Conservation) ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ መሆኑን መገምገም፤** | 15. የኢነርጂ ቁጠባ ደንብና መመሪያዎች (Energy Conservation Rule And Regulation) ሊዘጋጅና በሚመለከተው አካል ጸድቆ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 16. ኃይል ቆጣቢ የሆኑ መሳሪያዎችን መጠቀም የሚያስችል የኢነርጂ አጠቃቀም ደረጃ (standared) ሊያዘጋጅና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 17. የሀገሪቱ የኢነርጂ ፍላጎት፣ ጥቅም ላይ የዋለ እና ያልዋለ የኢነርጂ መጠን በባለስልጣን መ/ቤቱ ሊታወቅ ይገባል፡፡ |
| | 18. ባለስልጣን መ/ቤቱ የኢነርጂ መጠቀሚያ ቴክኖሎጂዎችን ለመለየትና የኢነርጂ አጠቃቀምን ማወቅ የሚያስችል የመነሻ ጥናት (Baseline) ሊያካሂድ እና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡ |
| | 19. ኢነርጂ ቆጣቢ የሆኑ የኢነርጂ መጠቀሚያ ቴክኖሎጂዎችን ለገበያ ከመቅረባቸው በፊት የሚያሟሉት ደረጃ ታውቆ በየመሣሪያዎቹና ዕቃዎቹ ላይ ደረጃቸውን የሚገልጽ የተለጣፊ ምልክት እንዲለጠፍ ለአቅራቢዎቹ የሚያረጋግጥ ፈቃድ ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| | 20. ባለስልጣን መ/ቤቱ የኢነርጂ ቁጠባ ፕሮግራም ሊያዘጋጅና አፈጻጸሙንም በወቅቱ ሊገመግም ይገባል። |
| | 21. በስራ ላይ የዋለውን የኢነርጂ ቁጠባ ፕሮግራም አፈጻጸም ያስገኘውን ተጽዕኖ መለካት የሚያስችል የግምገማ ጥናት (Impact Assessments) ሊደረግ ይገባል። |
| 3. **የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ስራዎችን ውጤታማ ለማድረግ)፣ ክትትልና ድጋፍ፣ ቅንጅታዊ አሰራር እና የመረጃ አያያዝ ስርዓት መኖሩን እና ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፤** | 22. ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በየዘርፉ (በኢንዱስትሪዎች፣ ሆቴሎች፣ ሆስፒታሎች እና ሌሎች) ከፍተኛ የኢነርጂ ተጠቃሚ አካላት የኢነርጂ አጠቃቀም ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ከመርሃ-ግብሩ አንፃር የመገምገምና ውጤቱን የማሳወቅ (ለውሃ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር፤ለህዝብ ተወካዮች ፤ለተፈጥሮ ሀብት ልማትና አከባቢ ጥበቃ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ወ.ዘ.ተ) ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡ |
| | 23. በኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ዘርፍ ለሚሳተፉ የኢነርጂ ተጠቃሚ ተቋማት የቴክኒክና የፋይናንስ ድጋፍ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 24. በተመረጡና ከፍተኛ የኢነርጂ አጠቃቀም ደረጃ ባላቸው ተቋማት ላይ የኢነርጂ ኦዲት ሊደረግ እና ግብረ መልስ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ |
| | 25. በኢነርጂ ኦዲቱ ወቅት ጉልህ ግኝት የተገኘባቸው ላይ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 26. ባለስልጣን መ/ቤቱ በኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ የኢነርጂ አጠቃቀምን አስመልክቶ ከከፍተኛ የኢነርጂ ተጠቃሚ አካላት የኢነርጂ አመራር የስራ ክፍል (Energy Management Unit) እንዲያቋቁሙ ለማድረግ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ሊሰራ ይገባል። |

| የኦዲት ጭብጥ (Audit Issues) | የኦዲት የመመዘና መስፈርቶች (Evaluative criteria) |
|---|---|
| | 27. ባለስልጣን መ/ቤቱ ከኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ጋር የተዛማጅ የሆኑ መረጃዎችን ሊሰበስብ፤ ሊተነትን፤ ሊያደራጅ እና ለሚመለከተው አካል ሊያሰራጭ ይገባል፡፡ |
| | 28. የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ አስፈላጊነት ዙርያ ለኢነርጂ ለተጠቃሚዎችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በተለያዩ መንገዶች (በኤሌክትሮኒክ ሚዲያዎች፣ በብሮሸሮች፣ ቢልቦርዶች እና በአካል ስልጠና በመስጠት) የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ሊሰሩ ይገባል፡፡ |
| | 29. ባለስልጣን መ/ቤቱ የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ሰርቶ ማሳያ ሊያስፋፋና ሌሌችም ይህንኑ ተግባራዊ እንዲያደርጉ ሊያስተባብር ይገባል፡፡ |
| | 30. ባለስልጣን መ/ቤቱ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባን በሚመለከት ከሚመለከታቸው መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ መ/ቤቶች እንዲሁም የኢነርጂ ተጠቃሚ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር ሥርዓት ሊኖረውና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል። |
| | 31. ባለስልጣን መ/ቤቱ ግብዓት ሊሆኑ የሚችሉ መረጃዎችን በማቅረብ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ በብሄራዊ የትምህርት ስርዓት እንዲካተት ጥረት ሊያደርግ ይገባል። |
| | 32. ከታዳሽ ኢነርጂ ምንጮች ኢነርጂ አመንጭተው ለሚሸጡ ተቋማት ወይም ግለሰቦች ድጋፍ (ከቀረጥ ነፃ፣ የቴክኒክ፣ የፋይናንስ እንዲሁም የስልጠና) ሊደረግ ይገባል፡፡ |

## አባሪ 2: የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለሥልጣን ድርጅታዊ መዋቅር



## አባሪ 3፡

## በናሙና ተመርጠው የታዩት ከፍተኛ ኢነርጂ ተጠቃሚ ተቋማት

### ፋብሪካዎች

1. ቢጂአይ ኢትዮጵያ፣
2. አቃቂ ብረታ ብረት ፋብሪካ፣
3. ሆራይዘን አዲስ ጎማ ፋብሪካ፣
4. ሞሃ ለስላሳ መጠጦች ኢንዳስትሪ ወይም ንፋስ ስልክ ፋብሪካ፣
5. ኢስት አፍሪካ ቦትሊነግ፣
6. አይካ አዲስ ቴክስታይል ኤንድ ኢቨስትመንት ግሩፕ፣
7. ሙገር ስሚንቶ ፋብሪካ፣
8. ኮምቦልቻ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ እና
9. ደብረብርሃን ብርድ ልብስ ፋብሪካ

### ሆስፒታሎች

1. ፖሊስ ሆስፒታል፣
2. ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል፣
3. አለርት ሆስፒታል፣
4. ቅዱስ ገብርኤል ሆስፒታል እና
5. ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል

### ሆቴሎች

1. ሸራተን አዲስ ሆቴል፣
2. ሂልተን ሆቴል፣
3. ግዮን ሆቴል፣
4. ጁፒተር ሆቴል እና
5. አራራት ሆቴል